# እንኩአን አደረሰህ አትበሉኝ

መስከረም1/2005

እንኩዋን አደረሰህ አትበሉኝ
ቁስሌን በሽታዬን አትነካኩኝ
ልርሳው አባካችሁ አትቀስቅሱኝ
የወገኔ መከራ ችግር በርክቶ
ዘመናትን የሞት ሞቶ
80ሚሊየን ህዝብ ተኮራምቶ
የሚቀምሰው የሚበላው አጥቶ
የበይ ተመልካች በመሆኑ
ተዘንግቶ ሰው መሆኑ
ተረግጦ ተንቆ በወገኑ
ተዲያ የምን አዲስ ዘመን
አሮጌው ላይ ተቀምጠን
ፍቅር ሰላምን አጥፍተን
ጥላቻ ዘረኝነትን አንግሰን
ዘመነ ማቲዎስ ላይ ደረስን
ከአምላክ እና ከሰው ለተጣሉ
80 ሚሊየን ህዝብ ረግጠው ለሚበሉ
እንኩአን አደረሳችሁ እነሱ ይባሉ
እንኩአን አደረሰህ እርግማን ሆኖብኝ
ችግርና መከራው ወድቆብኝ
የሚያድነኝ ሰው ጠፍቶብኝ
ይህው ዘመነ ማቲዎስ ላይ ደረስኩኝ
ዘመነ ዮሀንስ አሳይቶኝ ያልጨረሰው
አናት አናቱን የቀጠፈው
ከስሩ ተንቅሎ ያልወደቀው
የአዳምን ዘር የበተነው
ዘመነ ማቲዎስ ቢጨርሰው
ደስታ ፈንጠዝያውን እናቆየው
እንኩአን አደረሰህ አትበሉኝ
እንደሌለሁ እንዳልነበርኩ እርሱኝ
ይህን ዘመን ታገሱኝ
2012/11sap ወንድወሰን ሰብስቤ
Cov england